አንተ ማነህ?

ሁሉም ክርስትያን
ሊመልሰው የሚያስፈልግ
ጥያቄ

ሞሰስ ሲ. አንጂቢኮ

በኢትዮጵያ ገነት ቤተክርስቲያን

ትርጉም

መጋቢ ጎሣዬ ዓለሙ

አርታኢ

ወ/ም ዳዊት ዱኪ (እንግሊዝኛ)

ወ/ም አምበርብር ገብሩ (አማርኛ)

አድራሻ፡- ፓ. ሣ. ቁጥር 28683

አዲስ አበባ

ኢሜይል፡- visitegc@gmail.com

"እውነትን ግዛ አትሸጣትምም፥"
(ምሳሌ 23፡23)

በእርግጥ እውነትን (ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት) ለማወቅ ከባድ ነው፤ ሆኖም እግዚአብሔር ማለቂያ በሌለው ፀጋው ወደ እውነት ከመራህ፤ አንተ ከፍተኛ ዋጋ ሰጥተህ ልትቀበለው ይገባሃል። አንተም ለዘላለማዊ ሕይወትህ፤ ለደስታህ፤ ለጊዜያዊው በረከትህ ስትል አጥብቀህ መያዝ አለብህ።

አንተ የምትተኛ ንቃ፣ ራስህን ቀና አድርግ
ለኛ የታቀደልን ከዚህ የሚበልጥ ነው
ሞትን ለማሸነፍ ጥላዎቹን ተዋጋቸው
ጊዜህን ቀሪ ዘመንህን በሚገባ ተጠቀም

እኛ የዓለም ብርሃን ነን
እኛ በተራራ ላይ ያለች ከተማ ነን
እኛ የዓለም ብርሃን ነን
ተነስተን እናብራ[1]

1 WE ARE by Ed Cash, James Tealy, Chuck Butler & Hillary McBride © 2011

ያለ ክርስቶስ ነህ?

ወደ መንግስተ ሰማይ የሚሄደው አውሮፕላን ለመነሳት ተዘጋጅቶአል። አንተን ትቶ ሊሄድ ነው፤ ካልተሳፈርከበት መንግስተ ሰማያትን ታጣለህ፤ ከእግዚአብሔር ተለይተህ በእሳት ባህር ውስጥ ዘላለምን ታሳልፋለህ። (ራዕይ 20፡15) ይህ ላንተ ጥሩ ዜና አይደልም።

ረጋ በል! ነገሩ በመጥፎ ዜና አያልቅም፤ ወደ መንግስተ ሰማይ ለመጓዝና በዚያ ለማረፍ ፍላጎት ላላቸው ሁሉ ተወዳዳሪ የሌለው ፀጋ ያለው አምላክ መንገድ አዘጋጅቶአል። በልዩ ሁኔታ የተወለደውን አንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ለኃጢአታችን መሥዋዕት አድርጎ አቅርቦልናል። ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአታችን መሥዋዕት ሆኖአል። "ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።" (ሮሜ 5፡8) ለኃጢአት የሚከፈለው ዋጋ ሁሉ ተከፍሎአል። "ተፈጽሞአል" (ዮሐ. 19፡30) ይህ ድርጊት በጉዞአችን ያለ ምንም ችግር እንድናርፍ ያደርገናል። ለማረፍ ከአንተ የሚያስፈልገው አንድ ግዴታ ብቻ ነው። ይህም በኢየሱስ ክርስቶስና በመስቀሉ ሥራ ማመን ነው። "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" (ዮሐ. 14፡6)

ታዲያ አንተ በመንግስተ ሰማያት ለማረፊያ የሚያስፈልገውን በኢየሱስ የቀረበልህን ማለፊያ ለመቀበል ፈቃደኛ ነህ? ይህም በጣም ቀላል ነው፤ እምነትህን በክርስቶስ ላይ ማድረግ ብቻ ነው። "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ" (የሐዋ. 16፡31) አሉት። በእውነቱ ይህ መልካም ዜና ነው። በክርስቶስ አሁኑኑ

እምነትህን አድርግ ለመንግስተ ሰማያት ማለፊያና ማረፊያህ ለዘላለም የተጠበቀ ይሆናል።

በኢየሱስ ክርስቶስ ያመንክ ነህ?

ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ሕብረት፣ በአዕምሮህ (መጥፎ ሐሳቦች) በቃልህ (መጥፎ ቃላት) በድርጊት (መጥፎ ድርጊት) ያለመቋረጡን መፈተሽ አለብህ። ተበላሽቶ ከሆነ እግዚአብሔር የተበላሸውን ግንኙነት ለማደስ ፀጋውን አዘጋጅቶአል። "በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።" (1ዮሐ. 1:9) በቀላሉ ኃጢአትን ለእግዚአብሔር ብቻ ማሳወቅ ነው። እርሱ ታማኝ ነው።

❋ ❋ ❋

እባክህ ሰማያዊ አባት ሆይ ይህን መጽሐፍ የሚያነቡትን "በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው።" እባክህ እውነትህ ጠልቆ በመግባት እንዲለውጠንና ለክብርህ ምስጋናን እንዲያመጣ ድንቅ በሆነው በልጅህ በኢየሱስ ስም ፀልያለሁ።

አሜን!!!

"እኛ ለዓለም ያለብን ትልቅ ኃላፊነት ስለ
እግዚአብሔር ትከከለኛ ግንዛቤ መስጠት ነው"

⁂

ጆን ዊስሊ
1703 - 1792 (እ. አ. አ)

መግቢያ

እንተ ማነህ? በእግዚአብሔር የተወደድክ ጊዜው በጣም እየፈጠነ ነው። ጥቂት ቆም ብለህ ትክክለኛ ጥያቄ በመጠየቅ እውነተኛ ሕይወትህን መፈተሽ ያስፈልግሃል። እኔ ማነኝ? የት ነው ያለሁት? ምድር በምትባለው ፕላኔት ላይ ለምን ኖርኩ? ጌታዬ እንደሚፈልገው ተልዕኮዬን እያሟላሁ ነው? አምላኬ ከሰጠኝ ቀናት ምንያህል ጊዜ ቀርቶኛል?

መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ነገር ግልጽ ነው፤ የእንተ "ዕድሜ የተወሰነ ነው፥" (ኢዮብ 14፡5) እንተ "ዘመንህ በምድር ላይ እንደ ጥላ ናት፥" (ዘዳ. 29፡15) ጥላ አሁን በዚህ ደቂቃ እዚህ ነው ስንለው፤ በቅጽበት ይጠፋል። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንድም ያዕቆብ ከዚህ ሐሳብ ጋር ይስማማል። "ሕይወታችሁ ምንድር ነው? ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁና።" (ያዕቆብ 4፡14)

አንድ ጊዜ የጌታ ደቀ መዛሙርት "ጌታ ሆይ፥ ኤልያስ ደግሞ እንዳደረገ አሳት ከሰማይ ወርዶ ያጥፋቸው (ሰማርያውያንን) እንል ዘንድ ትወዳለህን?" (ሉቃስ 9፡54) አሉት። ጌታ የመለሰላቸው ምላሽ የኛን ትኩረት የሚገዛ ነው፤ "እርሱ ግን ዘወር ብሎ ገሠጻቸውና፦ ምን ዓይነት መንፈስ እንደ ሆነላችሁ አታውቁም፤" (ሉቃስ 9፡55) ቀለል አድርገን ስንተረጉመው "ማን እንደሆናችሁ ምንም ፍንጭ የላችሁም" ማለቱ ነበር።

አንተ ማነህ? ይህ ጥያቄ ትንሽ ይመስላል እንጂ ትልቅ ጥያቄ ነው። ክርስቲያኖች በአብዛኛው ማን እንደሆኑና፤ ተልዕኮአቸው ምን እንደሆነ አያውቁም። ይህ ደግሞ የቤተ ክርስቲያንን ምስክርነት ጎድቶአል፤ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ከምን

ጊዜውም በላይ ጎድቶኢታል። በሕይወት ሁለቱን ነገሮች ማለትም አንተ በክርስቶስ ማን እንደሆንክና ተልዕኮህ ምን መሆኑንን በደንብ የራስህ እስካላደረክ ድረስ እግዚአብሔር ያቀደልህን ልትፈጽም አትችልም።

በዚህ ጥናት ጎላ አድርገን የምንመለከታቸው ዘጠኝ ነገሮች አሉ፣ እንደኛ አንተ በክርስቶስ ያለህን ሥፍራ ያሳውቅሃል፤ ሁለተኛ አግዚአብሔር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ለምን በአንተ ውስጥ እንዳደሩ ታውቃለህ፤ ሦስተኛ አንተ የዓለም ብርሃን ነህ (ማቴ. 5፡14) ማለት ምን ማለት እንደሆነ የበለጠ ግንዛቤ ታገኛለህ፤ አራተኛ አንተ የምድር ጨው ነህ የሚለውን ትርጉም እንፈልጋለን። (ማቴ.5፡13) አምስተኛ ቸል የተባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ከፍልና አነጋጋሪ የሆነውን "ደብዳቤዎቻችን ናችሁ" የሚለውን እንመረምራለን። (2ቆሮ. 3፡2) ስድስተኛ ሐዋርያው ጳውሎስ "በሚድኑቱና በሚጠፉቱ ዘንድ ለእግዚአብሔር የክርስቶስ መዓዛ ነንና፤" (2ቆሮ. 2፡15) ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ እንፈልጋለን፤ ሰባተኛ ሕያው የሆነውን የእግዚአብሔር ፍቅር አማኞች እንዴት ማሳየት አንዳለባቸው እንገልጻለን፤ ስምንተኛ ክርስቲያኖች የሰላም አርማ መሆናቸውን በግልና በጋራ /በሀገር ደረጃ/ ያላቸውን ሐሳብ እናሳድጋለን፤ ዘጠነኛ ክርስቲያኖች የበረከት ማስተላለፊያ ናቸው የሚለውን ሐሳብ እናብራራለን። እነዚህንና ሌሎችን ርዕሶችን በዚህ ጥናት እናያለን። አሁንም እንጠይቃለን አንተ ማነህ?

እኔ ማን ነኝ?

ቁጥር ፩. አንተ በክርስቶስ ነህ

በክርስቶስ ያለህ ሥፍራ አንተን አዲስ ፍጥረት፣ የእግዚአብሔር ልጅ፣ ከክርስቶስ ጋር ወራሽ አድርጎአል። "ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው" (2ቆሮ. 5፡17) ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚነግረን እንደ እግዚአብሔር ልጅ እኛ "የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፣ ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን።" (ሮሜ 8፡17) የሕዋ ፈጣሪ የሆነው አምላክ እና ከተወደደው ልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ወራሽ መሆንህን ጥቂት ቆም ብለህ ልታስበው የሚገባው ሐቅ ነው። አንተ የክርስቶስን ጥበብ፣ ጽድቅ፣ ቅድስናና ሌሎችም የበለጡ ነገሮች ተካፋይ ነህ። (1ቆሮ. 1፡30)

አንተ የታወቅህበት የእግዚአብሔር ልጅነትህ "በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ" (ኤፌ. 1፡3) እንድትካፈል ተሰማሚ አድርጎአል። ይህ ማለት ሰማያዊ በረከት በአንተ ላይ ይመነጫል ማለት ነው። መረዳት የሚገባህ ነገር አንተ የእግዚአብሔር ዓላማ ነህ በክርስቶስ ካገኘኸው ሥፍራ የተነሳ ሁሉም መንፈሳዊ በረከት ያበረታታሃል መንፈሳዊ ሕይወትም ላይ ጠንቃቃ ያደርግሃል። በክርስቶስ የሆኑ ሰዎች ክርስቲያን የሚለውን ስም አስገኝተዋል። በብዙ ባህሎች ውስጥ ስሞች በጣም አስፈላጊዎችና ትርጉም ያላቸው ናቸው። ክርስቲያን የሚለው ስም ከየት መጣ ምን የሚያመለክተው ነገር አለ?

ክርስቲያን

በዘመናዊው ክርስትና ክርስቲያን የሚለው ቃል እንደ ቀላል እየተጠቀሙበት ነው። ስያሜውን የሰጡት የኢየሱስ ተከታዮች ሳይሆኑ ባልዳኑ አረማውያን ነው። የተገኘው "ክርስቲያኖስ" ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም የክርስቶስ ባሪያ ማለት ነው። ጥቅም ላይ የዋለው የክርስቶስ ተከታዮችን ከቄሳር ተከታዮች ለመለየት ነው። በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ይጠቀሙበት የነበረው ለማፈዝ[2] ነበር። ነገር ግን ከሚሰጠው ትርጉም የተነሳ ተጠሪዎቹ ሞገስ አግኝተውበታል። በአንጾኪያ የነበሩት አረማውያን የተመለከቱት ነገር ቢኖር እነዚህ የክርስቶስ ተከታዮች አንድነትና እንዳቸው ለሌላቸው ይጠነቀቁ እንደነበረ ነው። "በመካከላቸው አንድ ስንኳ ችግረኛ አልነበረምና፤ መሬት ወይም ቤት ያላቸው ሁሉ እየሸጡ የተሸጠውን ዋጋ ያመጡ ነበርና፥ በሐዋርያትም እግር አጠገብ ያኖሩ ነበር፤ ማናቸውም እንደሚፈልግ መጠን ለእያንዳንዱ ያካፍሉት ነበር።" (የሐዋ. 4፡34-35) ክርስቶስ በመጀመሪያ ምጽአቱ ጊዜ እንዴት እንደኖረ እነዚህ አረማውያን በክርስቶስ ተከታዮች የዕለት ተዕለት ኑሮ በመመልከት ፍቅራቸው ከነሱ አልፎ በውጪ ባሉት ዘንድ ተጽዕኖ አሳድሮ ነበር። የክርስቶስ ፍቅር ለሰው ሁሉ መሆኑን ለማስታወስ ችለው ነበር ሩኅሩኅነቱ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሳይቀር በጎ እንዲሆኑ አድርጎ ነበር። ተከታዮቹም ልክ እንደ እርሱ

2 Wuest, Kenneth Samuel, Wuest's word studies from the Greek New Testament.Wm. B. Erdmans Publishing, (1973) p.19

ሆነው ስላገኙአችው ክርስቲያኖች አሉአቸው፡- እንደ ኢየሱስ የሚያደርጉ፡፡ አንተ እውነተኛውን የክርስትና ኑሮ እየኖርክ ነው? አባክህ ይህን ጥያቄ ወደ ጎን አራግፈህ አትሰፈው የጥያቄው ምላሽ በአሁኑና በዘላለማዊው በረከትህ ላይ ከባድ ተጽዕኖ አለው፡፡

አንተ ማነህ?

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. እኛ በክርስቶስ ነን ማለት ምን ማለት ነው? በክርስቶስ መሆን ምን ይጠቅማል?
2. እውነተኛ የክርስትና ኑሮ መኖር ማለት ምን ማለት ነው?

ቁጥር 2. አንተ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነህ

አንተ ለእግዚአብሔር እጅግ አስፈላጊ ነህ። እንዲያውም በጣም ጠቃሚ ሰው /VIP/ ነህ። አንተ ተራ ሰው ልትመስል ትችላለህ ግን አይደለህም። በእምነትህ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት /ገንቢነት/ የሕያው እግዚአብሔር ማደሪያ ነህ። (2ቆሮ. 6፡16) ምንም አይደለህም እያለ እንደ ምናምንቴ የሚቆጥርህን ሰይጣንን አትፍቀድለት። በተቃራኒው አንተ ለእግዚአብሔር ልዩ ነህ። "እንደ ዓይኑ ብሌን ነህ።" (ዘካ. 2፡8)

ብዙ ክርስቲያኖች አካላቸው የእግዚአብሔር ማደሪያ ነው ሲባል አይገባቸውም። "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? (1ቆሮ. 3፡16) ሁላችንም ይህን ጥያቄ ራሳችንን እንጠይቅ።

የቤተ መቅደስ አስፈላጊነት

ቤተ መቅደስ ቅዱስ የሆነው አምላክ ከሰው ጋር የሚገናኝበት ነው። የአምልኮ ሥፍራ ነው። (2ዜና. 7፡3) ቤተ መቅደስን ልዩ የሚያደርገው ነገር የእግዚአብሔር መገኘት ነው፤ የእግዚአብሔር ማደሪያ ነው። ሁለት ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቤተ መቅደሶች አሉ። የብሉይ ኪዳን ቤተ መቅደሶች በእጅ የተገነቡና የአዲስ ኪዳን ቤተ መቅደስ የአማኞች ሁሉ አካል፣ በመንፈስ ቅዱስ የተገነባ ነው።

የሰለሞን ቤተ መቅደስ

የሰለሞን ቤተ መቅደስ በባቢሎናውያን ከተደመሰሰ በኋላ በህዝቡ ተገነባ። በሰለሞን ቤተ መቅደስ አንድ ልዩ

ሥፍራ ወደ ውስጥ ሲገባ አለ፣ ቅድስተ ቅዱሳን ተብሎ የሚጠራ የቃል ኪዳኑ ታቦቱ ማስቀመጫ። እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ ታቦት ጫፍና ጫፍ ባሉት በሁለቱ ኪሩቤሎች መካከል እግዚአብሔር በቅድስተ ቅዱሳኑ ያድራል። (ነሳሙ. 4፡4) ሰለሞን ቤተ መቅደሱን በሚያስመርቅበት ጊዜ "የእግዚአብሔርም ክብር የእግዚአብሔርን ቤት ሞልቶት ነበርና ካህናቱ ወደ እግዚአብሔር ቤት መግባት አልቻሉም።" (2ዜና. 7፡2) የእግዚአብሔር መገኘት ለህዝቡ /ለእስራኤል/ ሰላም፣ ጥበቃ፣ መግቦት (መስጠት) ምሪት፣ የተትረፈረፈ በረከት ይወከላል።

በብሉይ ኪዳን ሕግ መሠረት ቤተ መቅደስ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው የአምልኮ ሥፍራ ነው። ኢየሱስ ሕግን ሲፈጽም አምልኮ የሚካሄድበት መንገድና ሥርዓት ተለወጠ። «በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል። (ቤተ መቅደሱ ባለበት) ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና፣ እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።» (ዮሐ. 4፡21፣ 23-24)

የሰው ቤተ መቅደስነት

በዓለ ሃምሳ ካመጣቸው ለውጦች አንዱ የእግዚአብሔር ዕቅድ ላይ ማደሪያውን ለውጦአል። ለውጡም አማኞች ሁሉ የእርሱ ማደሪያዎች መሆናቸው ነው። «እኛ የሕያው እግ ዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነን» (2ቆሮ. 6፡16) እግዚአብሔር የእንተን አምልኮ ይፈልገዋል፤ ስለዚህ መንፈስህ ለእርሱ ቅዱስ ሆኖ መለየት አለበት። እርሱም አዞናል፡-

ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ ርኩስንም አትንኩ ይላል፤ (2ቆሮ. 6፡17) በታጢአት እንደቆሸሸን ስናውቅ (1ዮሐ. 1፡9) ቅድስናችንን ሁልጊዜ በንስሐ ማደስ አለብን፤ በውስጣችን እግዚአብሔርን ሳናመልክ ከሌሎች አማኞች ጋር ውጪያዊ አምልኮ የውሸት ይሆንብናል። በሌላ መልኩ በውስጥ ያለው ቅድስተ ቅዱሳን ነፍሳችን በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ካልተለየ አምልኮ የለም። (ኤፌ. 5፡18)

አንተ ዓለምን ከእግዚአብሔር ጋር አገናኝ ነህ። በአንተ በኩል ክብሩን ለዓለም መግለጥ ይፈልጋል። «የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው።» (ቆላስ. 1፡27)

አንተ ማነህ?

የውይይት ጥያቄዎች

1. ሰው እንዴት የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ /ማደሪያ/ ሊሆን ይችላል?
2. እግዚአብሔር እንዴት ነው ክብሩን በኛ በኩል የሚገልጠው?

ቁጥር 3. አንተ የዓለም ብርሃን ነህ

«እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም» (ዮሐ. 8፡12) ብሎ ተናገራቸው። ወይስ (በማቴ. 5፡14) ኢየሱስ እንዳወጀው «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ።» ኢየሱስ ምን ማለቱ ይሆን? በቀላሉ የእርሱን ብርሃን ተሸካሚዎች ነን። እርሱ ብርሃን ነው። እርሱ በአንተ በኩል ያንጸባርቃል ወይም ያበራል። «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና» (ዮሐ. 15፡5) ሐዋርያው

ጳውሎስ ይህን የበለጠ ሲያብራራ «ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው፤» (2ቆሮ. 5፡18) ይላል።

ከጥቂት ዓመታት በፊት ወደ አፍሪካ ከከተማ ራቅ ወዳለ ሥፍራ ለሚሰዮናዊ ጉዞ ሄጄ ነበር። መብራት ከሚበራበት ጊዜ ይልቅ የሚጠፋበት ጊዜ ይበልጣል። አንድ ቀን በአንድ ቤተሰብ ቁጭ ብለን እራት እየበላን ሳለ ድንገት ድርግም አለ። ደቅደቅ ጨለማ ወረሰን የምግብ ሳህናችንን እንኳ ማግኘት አልቻልንም። ምግብ መመገባችንን ለማቆም ተገደድን። ከዚያ አንድ ሰው ተጠርቶ የጋዝ ፋኖስ አመጣና ብርሃን አገኘን። ደስታችን ጨመረ ራታችንን መብላት ጀመርን።

የአንተ ሥራ ብርሃን መስጠት ነው። ኢየሱስ እንደዚህ አለ፦ «መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።» (ማቴ. 5፡16) በቤት፣ በማህበረ ሰብህና በአገር ጨለማ ካለ የእግዚአብሔር ብርሃን እንዳያበራ የከለከልከው አንተ ነህ። አማኝ ያልሆኑ ሰዎች በፓዝዎች፣ በፖለቲከኞች፣ በፕሬዚዳንታቸው ወይም በጠቅላይ ሚኒስቴራቸው በብሔራዊ ደረጃ ስላለባቸው ነገር ቢያማርሩ ይቅር ይባላሉ። ነገር ግን አማኝ የሆነ ሰው ከእነርሱ ጋር ቢተባበር ተገቢ አይደለም። አማኞች የዓለም ብርሃን ናቸው፤ ፓዝዎች ግን አይደሉም። አንድ ሰው የእግዚአብሔር ብርሃን በሕይወቱ እንዳያበራ ቢያደርግ ምን ይሆናል? እግዚአብሔር ቅጣት በመላክ ትኩረታቸውን በእርሱ ላይ እንዲያደርጉ ያደርጋል።

ቅጣት እግዚአብሔር ልጆቹን የሚያስተካከልበት መንገድ ነው። «አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማን ነው?» (ዕብ. 12፡7) ማንም የለም። «እርሱ ግን ከቅድስናው እንድን ካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል።» (ቁጥር 10)

ጌታ ደቀ መዛሙርቱን ወንጌልን ወደ ኢየሩሳሌም፤ ይሁዳና ሰማርያ ከዘያም ባለፈ እንዲያደርሱ አዘዛቸው። (የሐዋ. 1፡8) መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ለመሄድ አመነቱ /ዘገዩ/። የእግዚአብሔር ምላሽ ግን ትዕይንታዊ ነው። የተቀነባበረ ስደት በማስነሳት እንዲንቀሳቀሱ አደረገ። «በዚያን ቀንም በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ፤ ሁሉም ከሐዋርያትም በቀር ወደ ይሁዳና ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ። የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ።» (የሐዋ. 8፡1፡4)

እርምት የሚመጣው ሦስት ተጨማሪ ነገሮችን ይዞ ነው፤ ማስጠንቀቂያ፣ የቅጣቱን መጠን መጨመርና በመጨረሻም አካሉን ማውደም ነው።

- **የማስጠንቀቂያ ዕርምት**

ቤተ መቅደሱን ለማያከብሩ ማስጠንቀቂያዎችን ይልካል። ስለዘህ በአናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ (1ቆሮ. 11፡30) ድካም በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለማመዱት የቅጣት ማስጠንቀቂያ ነበር። ከርስቲያኖች ማስጠንቀቂያውን ሥፍራ ካልሰጡት ወይም ችላ ካሉ እግዚአብሔር የቅጣቱን መጠን ይጨምርባቸዋል።

- **የዕርምት መጠን መጨመር**

እግዚአብሔር የዕርምቱን መጠን መጨመር ይጀምራል። የሚጨምረው የጤንነት ጉድለት፣ የገንዘብ ችግር ወይም ማንኛውም ዓይነት መከራ ሊሆን ይችላል። የአማኙን ቤተ መቅደስ ለማደስ ለእግዚአብሔር ይህ የመጨረሻ ዕድል ነው። ማስጠንቀቂያዎቹ ሁሉ ዋጋ ካጡ ወይም በቸልታ ከታለፉ እግዚአብሔር አማኙን ወደ ዘላለማዊው ቤቱ ይጠዋራል። (1ዮሐ. 5፡16)

- **የእካል ውድመት**

«ብዙ ጊዜ ተዘልፎ እንጉቱን ያደነደነ ድንገት ይሰበራል፣ ፈውስም የለውም።» (ምሳሌ 29፡1) ለዚህ ነው ጳውሎስ በዚህ መልክ የገለጸው «ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና /ማስጠንቀቂያ/ የታመሙ ብዙዎች /ለረኽቦም ጊዜ የታመሙ/ አሉ አያሌዎችም አንቀላፍተዋል። /የእካል ውድመት/» (1ቆሮ. 11፡30) የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስነታችሁን እንደ ቀላል አትመልከቱት፤ ከፍተኛ ዋጋ ሳትከፍሉ የእርሱ ቤተ መቅደስ መሆን አትችሉም። «ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፣ ያውም እናንተ ናችሁ።» (1ቆሮ. 3፡17) እግዚአብሔር የጸጋ አምላክ ነው። «ሞት የሚገባው ኃጢአት አለ፤» (1ዮሐ. 5፡16) ምናልባት አካሉ ወድሞ ይሆናል ነገር ግን ነፍሱ ይድናል። «እርሱ ራሱ ግን ይድናል» (1ቆሮ. 3፡15)

እግዚአብሔር የሥራ አምላክ ነው። አንተ በእርሱና በዓለም መካከል አገናኝ ነህ። ራሱን በአንተ በኩል ለዓለም መግለጽ ይፈልጋል። በአንተ እንዲሠራ ትፈቅድለታለህ?

የውይይት ጥያቄዎች

1. ለዓለም ብርሃን መሆን የምንችለው እንዴት ነው?
2. ሦስቱ የመለኮታዊ ዕርምት/ዲስፕሊን/ ደረጃዎች እነማናቸው?
3. እግዚአብሔር በሕይወታችን እንዲሠራ እንዴት መፍቀድ እንችላለን?

ቁጥር 4. እንተ የምድር ጨው ነህ

የምንኖረው በበሰበሰና ጣዕም በሌለው ዓለም ነው። ነገር ግን ጨው ካሉት ሁለት የማይገሰስና የማንነት ባህሪዎቹ ማለትም ጣዕም መጨመርና እንዳይበሰብስ የመከላከል ችሎታው መፍትሔ ይሰጣቸዋል። የሚያስደንቀው ነገር እግዚአብሔር እንተን ጨው አድርጎአል።

ጣዕም

ዳዊት ሲዘምር «እግዚአብሔር ቸር እንደ ሆነ ቅመሱ እዩም፤» (መዝ. 34:8) ይህ ግብዣ የእግዚአብሔርን መልካምነት ላላጣሙት ሰዎች ነው። ነገር ግን አንድ ሰው የማይታየውን አምላክ እንዴት ማጣጣም ይችላል? አንተ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ስለ ሆንክ በእግዚአብሔር ውስጥ ያለው መልካምነት በአንተ ውስጥ ስለ ተከማች በአንተ እግዚአብሔር ይህንን ያደርጋል። የምስራቹ በአንተ ያምራል። ለትዳር ኋጋርህ፤ ለልጆችህ፤ ለጎረቤትህ፤ ለሥራ ባልደረቦችህ፤ ለትምህርት ቤት ጓደኞችህ ጣዕሙ በአንተ ውስጥ ባለው ፀጋ፤ ርኅራኄ፤ ፍቅር፤ በጎነትና ምህረት

መድረስ አለበት። «እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤» (ማቴ. 5፡13)

ወጣት በነበርኩበት ጊዜ ከወንድሞቼና ከእህቶቼ ጋር አንድ ቀን ከብ ተቀምጠን ምግብ ስንበላ ከሾርባ ማቅረቢያው ትልቅ ሳህን ሁላችንም ጨልፈን ወስደን ስንቀምሰው ጨው ስላልነበረው ጣዕም አልነበረውም። እንዲ እህቴ ኧረ የጨው ያለህ ብላ ፉጫች አንደኛው ወንድማችን ወደ ጓዳ በመሮጥ ጨው ነው ብሎ ያሰበውን በእጁ የተቻለውን ያህል ዝቆ አመጣና ጨመረበት ነገር ግን ጣዕሙ ያው ነው ምንም አልተቀየረም። እህቴ መጠየቅዋን አላቋረጠችም እርሱም እየሮጠ ማምጣቱን ቀጠለ ነገር ግን የሾርባውን ጣዕም መቀየር አልተቻለም። እህቴ በጣም ተበሳጭታ የጨዉን ዕቃ አምጣልኝ አለቺው። ወንድሜም የጨው ዕቃ ነው ያለውን ይዞ መጣ። እህቴም ዘገን አድርጋ ቀመሰቺው። ምን እንደምትል ለመስማት የሁላችንም ዓይኖች በእሷላይ አፈጠጡ። ራስዋን ይዛ ይህ እኮ የበቆሎ ዱቄት ነው አለች። የሾርባው ጣዕም ለምን እንዳልተቀየረ ሰው ሁሉ የገባው ያንጊዜ ነው።

ጌታም "ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል? ወደ ውጪ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ወደ ፊት ለምንም አይጠቅምም።" (ማቴ. 5፡13) ያለው ትክክል ነው። አንተ ምን ዓይነት ጨው ነህ?

መጠበቅ /መከላከል/

እንደ ጨው የአንተ መንፈሳዊ ህይወት ለዓለም ሞራል /ሥነ ምግባር/ ዝቅጠት አስተማማኝ መከላከያ ነው። የጽድቅ መስፈን ከፉ እንዳይነሳ ያደርጋል፤ ጽድቅ ወደ ላይ

ሲወጣ ከፉ ይወድቃል። ወይም በተቃራኒው ከፉ ወደ ላይ ሲወጣ ጽድቅ ይወርዳል። "ጽድቅ ሕዝብን ከፍ ከፍ ታደርጋለች፤" (ምሳሌ 14፡34) አንተ ከርስቲያን ስለሆንክ የዓለምን የሞራል /የሥነ ምግባር/ ዝቅጠት ብትወቅስ ስሜት አይሰጥም። አንተ የምድር ጨው ስለሆንክ መከላከል የሚቻለው በአንተ በኩል ነው ካልሆነ ዓለም እንደ በሰበሰች ትቆያለች። አማኞች በሥርዓት ሲሄዱ ሌሎችም የሀገሬው ሰዎች የእነሱን ምሳሌነት ይከተላሉ።

አንተ ብርሃንና ጨው ነህ፤ ሀብረተሰቡ ብርሃንና ጨው ካላገኘ ምክንያቱ አንተ ሁለቱንም መሆን ስላቻልክ ነው። አንተ ለጽድቅ ያለህ አቋም ቤተሰብህን፣ ማህበረ ሰብህን ከዚያም ሀገርህን ለመባረክና ለመጠበቅ ያስችላል። "በጻድቃን ልማት ከተማ ደስ ይላታል፥ በኃጥኣንም ጥፋት እልል ትላለች። በቅኖች በረከት ከተማ ከፍ ከፍ ትላለች፤ በኃጥኣን አፍ ግን ትገለበጣለች።" (ምሳሌ 11፡10-11) የእንተ መንፈሳዊ ሕይወት ለሀገር ማንባታ አስተዋጽዎ ያደርጋል ወይስ አፍራሽ ወይም አውዳሚ ነው?

አንተ ማነህ?

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. በምድር ላይ ጨው መሆን ማለት ምን ማለት ነው?
2. ጨው መሆናችንን የት የት ሊገለጥ ይችላል?

ቁጥር 5. አንተ አምስተኛው ወንጌል ነህ!!!

ሁሉም አንተን ያነብሃል "ሰዎች ሁሉ የሚያውቁትና የሚያነቡት በልባችን የተጻፈ መልእክታችን እናንተ ናችሁ።" (2ቆሮ. 3፡2) ብዙ ሰዎች የማቴዎስ፣ የማርቆስ፣ የሉቃስና የዮሐንስን ወንጌል ለማንበብ ሥራ ይበዛባቸዋል፤ ነገር ግን አንተን ለማንበብ ጊዜ አላቸው። አንተን በማየት ሕይወቱ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መንጌል የተለወጠ አንድ ሰው ማስታወስ ትችላለህ? እንድ ጊዜ አንድ ሰባኪ እንደዘህ አለ "ሕይወታችን ሰዎችን ወደ ኢየሱስ ያመጣቸዋል ወይም ያሳምፃቸዋል" ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን እውነት በምሳሌ አረጋግጦልናል፤ በሮማውያን የአገራረፍ ሥልት ሠላሳ ዘጠኝ ጊዜ ተገርፎ በወህኒ ተጥሎአል። (የሐዋ. 16፡23)

ከሕግ አንጻር ስንመለከተው ጳውሎስ የሮማዊ ዜግነት ስላለው ሲገረፍ አይገባውም ነበር። አስር ቤት ሲገባም አላጉረመረመም፤ አልነቀፋቸውም። ጳውሎስና ሲላስ በአስር ቤት በደስታ ባሕር ይፍለቀለቁ ነበር። "በመንፈቀ ሌሊት ግን ጳውሎስና ሲላስ እየጸለዩ እግዚአብሔርን በዜማ ሲያመሰግኑ እስረኞቹም ያደምጡአቸው ነበር" (የሐዋ. 16፡25) ይህ ደስታ ለነሱ ብቻ ሳይሆን እስረኞችን ወደ እነርሱ የሳበ ነበር። እስረኞቹ ጳውሎስን አንብበውት አምስተኛ ወንጌል ሆኖላቸው ነበር።

እግዚአብሔር ተአምራዊ በሆነ መንገድ የወህኒውን ደጆች ከፍቶ የሁሉም የእጆቻቸው ሰንሰለት ተፈታ፤ጳውሎስና ሌሎቹም ለማምለጥ አልሞከሩም። (የሐዋ. 16፡26-27) የጳውሎስና የሲላስ ታማኝነት ሁሉንም እስረኞች ታማኞች አደረጋቸው። የእስር ቤቱ አለቃ ራሱን ለመግደል ሲፈልግ ጳውሎስ ጮሆ ከሞት አተረፈው፤ "የወኅኒውም ጠባቂ ከእንቅልፉ ነቅቶ የወኅኒው ደጆች ተከፍተው ባየ ጊዜ፥

እስረኞቹ ያመለጡ መስሎት ራሱን ይገድል ዘንድ አስቦ ሰይፉን መዘዘ። ጳውሎስ ግን በታላቅ ድምፅ፦ ሁላችን ከዚህ አለንና በራስህ ላይ ከፉ ነገር አታድርግ ብሎ ጮኸ።" (የሐዋ. 16፡28)

የሐዋርያው ጳውሎስና የሲላስ በመከራ ውስጥ ሆነው ታማኝነት፣ ፍቅር፣ ሰላምና ደስታ በማሳየታቸው እስረኞቹን ሁሉ ወደ ክርስቶስ መሯቸው። ስለዚህ እንዲህ ብለው እንዲጠይቁ አደረጋቸው፣ "ጌቶች ሆይ፣ እንድን ዘንድ ምን እናድረግ አሉ?" (ቁጥር 30) የጳውሎስ ምላሽ በጣም ቀላል ነበር። "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመኑ ትድናላችሁ" አላቸው። (ቁጥር 31)

ሰዎች በአንተ ሕይወት የእግዚአብሔርን መልካምነት፣ ጸጋ፣ ምህረት፣ በጎነትና ፍቅር እነዚህን አስደናቂ ነገሮች አስካላዩ ድረስ ስለ እግዚአብሔር የመናገር ጉልበት አይኖርህም። ጳውሎስ፣ ሲላስና ጢሞቴዎስ ለተሰሎንቄና ለኛ ምሳሌ እንደሆኑልን እኛም ለሌሎች የክርስቶስ ምሳሌዎች መሆን አለብን። "ይህም እኛን ልትመስሉ ራሳችንን እንደ ምሳሌ እንሰጣችሁ ዘንድ ነበር" (2ተሰ. 3፡9)

ሐዋርያው ጴጥሮስ ኢየሱስን ለሌሎች የመግለጽን ነገር ተረድቶ ስለነበር፣ እንደዚህ አለ "ስለሚመለከቱት ስለ መልካም ሥራችሁ፣ ከፉ እንደምታደርጉ በዚያ እናንተን በሚያሙበት ነገር፣ በሚጎበኝበት ቀን እግዚአብሔርን ያከብሩት ዘንድ በአሕዛብ መካከል ኑሮአችሁ መልካም ይሁን።" (1ጴጥ. 2፡12)

የአንተ ሕይወት ከሁሉም በላይ ምርጡ የእግዚአብሔርን ቃል ገላጭና ተጽዕኖ ፈጣሪ ነው።ፍቅርን በዕብራይስጥ፣ በግሪክ በአርማይክ ብሎ ከመግለጽ ይልቅ ፍቅርህን አሳይ። በአቅራቢያህ ያለ ብዙ ነገሮችን የሚፈልግ አንድ ድሃ ስለግሪክና ዕብራይስጥ ትርጉም እንዲረዳ ከባድ ከምታደርግበት

ተግባራዊ ፍቅርህን አሳየው። አንተ አምስተኛው ወንጌል ነህ ሁሉም ሰው በየዕለቱ ያነብሃል።

አንተ ማን ነህ?

የውይይት ጥያቄዎች

1. ሰዎች የሚያነቡን እንዴት ነው?
2. ከጳውሎስና ከሲላስ ምን እንማራለን?

ቁጥር 6. አንተ የክርስቶስ መዓዛ ነህ!!!

አንተ ልዩ ነህ "የንጉሥ ካህን" (1ጴጥ. 2:9) የክርስቶስ ሐዋርያ (2ቆሮ. 3:2) እና "የክርስቶስ መዓዛ ነን" (2ቆሮ. 2:15) አንተ መያዣው ነህ ክርስቶስ መዓዛው ነው። "በሚድኑቱና በሚጠፉቱ ዘንድ" (2ቆሮ. 2:15) በአንተ በኩል ክርስቶስ መዓዛው እንዲያውድ ያደርጋል።

ሐዋርያው ዮሐንስ ይህን ለማስታወስ የማርያምን ፍቅር ይገልጻል። "ማርያምም ዋጋው እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱ ንጥር ወስዳ የኢየሱስን እግር ቀባች፥ በጠጒርዋም እግሩን አበሰች፥ ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ ሞላ።" (ዮሐ. 12:3) የአንዲት ትንሽ ብልቃጥ የናርዶስ ሽቶ ዋጋ ከአንድ ዓመት ደመወዝ ጋር ይመጣጠናል። (ዮሐ. 12:6፥ ማቴ. 20:2) የኢየሱስ ክርስቶስ መዓዛ ምን ያህል የሚያወጣ ይመስልሃል? ዋጋውን መተመን አይቻልም። በተገኘህበትና በምታገኛቸው ጓደኞችህ አካባቢ የክርስቶስ መዓዛ እንዲሸት ማድረግ አለብህ። ምን ዓይነት መዓዛ ነው የለበስከው ብለው እንዲደነቁና እንዲጠይቁ ማድረግ አለብህ። በሌላ መልኩ ይህ ማለት አንተ የክርስቶስ አምባሳደር /መልዕክተኛ/ ነህ ማለት ነው። (2ቆሮ. 5:20)

ሰዎች በእንተ አካባቢ ሲሆኑ የመንግሥተ ሰማያት የመዓዛ ሽታ ማሽተት አለባቸው::

እንድ መጥፎ ሽታ ባለበት ሰው አካባቢ ሆነህ አታስተህ ታውቃለህ? አንድ ጊዜ እኔን በአሳንሰር /በሊፍት/ ውስጥ ገጥሞኛል ሰውዬው የተቀባው ሽቶ በጣም መጥፎ ሽታ ነበረው፤ ስለዚህ አንቆ የገደለኝ ያህል ተሰምቶኝ ነበር:: በሚቀጥለው ወለል /ፎቅ/ ላይ ባይወርድ ኖሮ እኔ ወርጄ ንጹህ አየር ፍለጋ እዞር ነበር:: አንተም እንደዚህ ዓይነት በሆነ ሁኔታ ሆነህ ታውቃለህ ብዬ አስባለሁ:: እንተ ምን ዓይነት መዓዛ /ሽታ/ ያለው ሽቶ ነህ? ሰዎችን ወደ እንተ የሚስብ ጥሩ መዓዛ ያለው ሽቶ ነህ ወይስ ንጹህ አየር ፍለጋ ሰዎች ከእንተ እንዲሸሹ የሚያደርግ ነህ? ምላሹ በእንተና በአዳኝህ ሁሉን በሰጠህ ጌታህ መካከል የሚመለስ ነው::

እንተ ማነህ?

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ማርያም ለኢየሱስ ምን አደረገች?
2. ባለንበት ስፍራ እንዴት የክርስቶስ መዓዛ መሆን እንችላለን?

ቁጥር 7. አንተ ፍጹም የሆነው የክርስቶስ ፍቅር ገላጭ ነህ!!!

አጋፔ የተባለው ፍቅር ክርስቲያኖችን ከሌላው ዓለም ይለያቸዋል። አጋፔ ልዩ ፍቅር ነው። "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" (1ዮሐ. 4፡8) እግዚአብሔር አንተን የመረጠህ በአንተ በኩል ለሰው ዘር ሁሉ የላቀ ፍቅሩን ለመግለጥ ነው።[3] እግዚአብሔር በአንተ ውስጥ የመሆኑ መገለጫ ነው፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ፍቅሩን ይገልጣል። "ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው" (ገላ. 5፡22) እግዚአብሔር ብቻ ያለውን አጋፔና አስፈሪ ፍቅር በአንተ ውስጥ እንዲታይ ለማድረግ መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜ ዝግጁ ነው። «እርስ በር ሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፣ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።» (ዮሐ. 13፡35) በዚህ መልኩ ልግለጸው በምትኖርበት አካባቢ ሰዎች የአንተን ክርስቲያንነት ሊያውቁ አይችሉም፤ ምክንያቱም አንተ እንደ ክርስቲያን ስለማትኖር ነው። ተመሳስለህ ከኖርክ ለመንፈሳዊ ሕይወት ግድ ከሌለህ በአግባቡ እንድትመላለስና ሥርዓት እንድትይዝ የማንቂያ ደወል ያስፈልግህ ይሆናል።«እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ /የአስተሳሰብ ለውጥ/ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፤ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው እወስዳለሁ።» (ራዕይ 2፡5) እባክህን መንፈስ ቅዱስ በቅጣት እስኪነቦኽህ ድረስ አትዘግይ። እኔም የምመክርህ በተለወጠ አእምሮ የክርስቶስን ኑሮ እንድትኖር ነው።

---

3 Onwubiko, Moses C. Shower of Christian Love, Jarico Press, Nashville, TN, 2012

የውይይት ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሌሎች እንዴት መግለጽ እንችላለን?

ቁጥር 8. አንተ የሰላም ሰንደቅ ዓላማ ነህ!!!

ዓለም ሰላምን ለማግኘት ብዙ ብትናፍቅም ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ ልታጣጥመው አልቻለችም:: ማንም ከክርስቶስ ውጪ ሰላምን ሊለማመድ አይችልም::የተባበሩት መንግሥታት እውነተኛ ሰላም መስጠት አይችልም፤ እግዚአብሔር ብቻ ነው ሰላምን መስጠት የሚችለው::

ብዙ ክርስቲያኖች ክርስትና ታላቅ ተጽዕኖ ሊፈጥር እንደሚችል ይዘነጋሉ:: ንጹህ ክርስትና ባለበት ሁሉ ሰላምን ያመጣል:: በዳግም ልደት ያልተገኘ የውስጥ ሰላም በውጪ ሊታይ አይችልም:: "እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ፤" (ሮሜ 5:1) በክርስቶስ ስትሆን አንተ የእግዚአብሔር የሰላም ሰንደቅ ዓላማ ነህ:: "የከብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው::" (ቆላስ. 1:27) "የሰላም አለቃ" (ኢሳ. 9:6) በአንተ ውስጥ አለ:: ይህ ማለት አንተ እንደ ክርስቲያን ስትኖር እግዚአብሔር ለአንተም በዙሪያህም ላሉት አስፈላጊውን ሰላምን ይሰጣል:: "የሰው አካሄድ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘው እንደ ሆነ በአርሱና በጠላቶቹ መካከል ሰንኳ ሰላምን ያደርጋል::" (ምሳሌ 16:7) ይህ ነገር በንጉሥ ኢዮሳፍጥ እውነት ሆኖ ታይቶአል:: "የአባቱን አምላክ ፈለገ፥ በትእዛዙም ሄደ፥" (2ዜና 17:4) የመንፈሳዊነቱ ውጤት አስደነገጠ "በይሁዳም ዙሪያ በነበሩ መንግሥታት

ሁሉ ላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ድንጋጤ ሆነ፥ ከኢዮሳፍጥም ጋር አልተዋጉም።" (2ዜና 17፡10) እግዚአብሔር ቃሉን ይጠብቃል። ተግባራዊ ከርስትና ብዙ ጥቅሞችን ያስገኛል፤ ይህ ደግሞ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የታየ እውነት ነው። "በይሁዳም ሁሉና በገሊላ በሰማርያም የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ ታነጹም፤ በእግዚአብሔርም ፍርሃትና በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት እየሄዱ ይበዙ ነበር።" (የሐዋ. 9፡31) ዶክተር ስፒሮስ ዞዲኤትስ ይህን እጅግ አስደናቂ የክርስቲያኖች በሰላም መደሰት ሲገልጹ «እስከ ነፍሰ ገዳዩ ወይም አራጁ ዲሺየስ (249 - 51 ዓ.ም.) ድረስ ክርስቲያኖችን በግዛቱ ሁሉ ያሳደደ መንግሥት አልነበርም»[4] ብለዋል። ይህ ማለት በየስፍራው ሁሉ ስደት አልነበርም ማለት አይደለም፤ የጥንት ክርስቲያኖችም ከስደት ነጻ አልነበሩም። እግዚአብሔር መከራን ልጆቹን ለማሳደግ ወይም ለማብሰል ይጠቀምበታል። (ዕብ. 5፡8-9)

እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ጉዞአቸው እርሱን ለሚያስደስቱ ሰዎች ሁለቱንም ማለት የውስጥና የውጪ ሰላምን ይሰጣቸዋል። እናንተ ግን በብሉይ ኪዳን ዘመን እንዳስደሰቱት ሰዎች ብትሆኑ (2ዜና 15፡3) እግዚአብሔር ብድራቱን በዓይነቱ ይመልስላችሁ ነበር። "በዚያም ዘመን ለሚወጣውና ለሚገባው ሰላም አልነበረም፥ በምድርም በሚኖሩት ሁሉ ላይ ታላቅ ድንጋጤ ነበረ። እግዚአብሔር በመከራው ሁሉ ያስጨንቃቸው ነበርና ወገን ከወገን ጋር፥ ከተማም ከከተማ ጋር ይዋጋ ነበር።" (2ዜና 15፡5-6)

የአንተ መንፈሳዊ ሕይወት ዋጋ አለው። ለአንተ፣ ለቤተሰብህ፣ ላለህበት ማህበረ ሰብና ለሕዝብ ሁሉ የበረከት

---

4 Zondhiates, Spiros Editor, Hebrew, Greek New Armenian Standard Bible, Chattanooga, TN 1995, p 1644

ወይም የዕርምት እርምጃ ምክንያት ይሆናል::

እንተ ማነህ?

የውይይት ጥያቄዎች

1. የሰላም ሰንደቅ ዓላማ መሆን የምንችለው እንዴት ነው?
2. ተግባራዊ ከርስትና የሚያስገኛቸው ጥቅሞች ምንድናቸው?

ቁጥር 9. አንተ የእግዚአብሔር በረከት ቢንቢ ነህ!!!

ከእግዚአብሔር የማመጣ በረከት ከእግዚአብሔር ባህርይ ጋር ይስማማል:: "የዙፋንህ መሠረት ጽድቅና ፍርድ ነው፤ ምሕረትና እውነት በፊትህ ይሄዳሉ::" (መዝ. 89:14) ሁለቱ የእግዚአብሔር በረከት ምክንያቶች የእግዚአብሔር ባህርያት ጽድቅና ፍትህ ናቸው::

እግዚአብሔር በረከቱን የሚሰጠው በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ነው፤ ምክንያቱም ክርስቶስ የእግዚአብሔር ጽድቅ መገለጫ ምሳሌ ስለሆነ ነው:: ክርስቶስ በአንተ ውስጥ በማያሩ አንተ የክርስቶስ በረከት ተካፋይ ነህ:: ይህ ሁኔታ የተገደበ ነው፤ በአንተ መመሪያዎችን መታዘዝ ላይ ይወሰናል:: እግዚአብሔርን የሚያከብር ሕይወት ስትኖር በልጁ በኢየሱስ በኩል በረከቱ ይፈስልሃል:: ከዚህ የተነሳ ለቤተሰብህ፤ ለማህበረ ሰብህና ለዓለም የበረከት ቢንቢ ትሆናለህ:: ይህ የማህበር በረከት ነው፤ ከአንተ የተነሳ እግዚአብሔር ለማይገባቸው ሰዎች እንኳን በረከቱን ይሰጣቸዋል::

በባሪያው በዮሴፍ ምክንያት ግብፅና እስራኤል የእግዚአብሔርን በረከት እንዴት እንዳገኙ አስተውለሃል!!!

"ዮሴፍ ግን ወደ ግብፅ ወረደ፤ የፈርዖን ጃንደረባ የዘበኞቹም አለቃ የሚሆን የግብፅ ሰው ጲጥፋራ ወደ ግብፅ ካወረዱት ከእስማኤላውያን እጅ ገዛው። እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበረ፥ ሥራውም የተከናወነለት ሰው ሆነ፤ በግብፃዊው ጌታውም ቤት ነበረ። ጌታውም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዳለና፥ የሚሠራውንም ሁሉ እግዚአብሔር በእጁ እንዳከናወነለት አየ። ዮሴፍም በጌታው ፊት ሞገስን አገኘ፥ እርሱንም ያገለግለው ነበር፤ በቤቱም ላይ ሾመው፥ ያለውንም ሁሉ በእጁ ሰጠው። እንዲህም ሆነ፤ በቤቱ ባለውም ሁሉ ላይ ከሾመው በኋላ እግዚአብሔር የግብፃዊውን ቤት ስለ ዮሴፍ ባረከው፤ የእግዚአብሔር በረከት በውጪም በግቢም ባለው ሁሉ ላይ ሆነ።" (ዘፍ. 39፡1-5)

አንተም ልክ እንደ ዮሴፍ በቤተሰብህና በሀገርህ ላይ ከፍተኛ ተጽህኖ ልታሳድር ትችላለህ። እንደ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወትንና ተጽህኖ መፍጠር መቻልህን ዋጋ እንደሌለው አትቁጠረው። "በቅኖች በረከት ከተማ ከፍ ከፍ ትላለች፤ በኃጥኣን አፍ ግን ትገለበጣለች።" (ምሳሌ ፲፡፲፩) የአንተ ተጽህኖ ፈጣሪነት አስደናቂ ሊሆን ይችላል፤ ስለዚህ ንቃ እንደ ክርስቲያን ኑር!!!

የውይይት ጥያቄዎች

1. እኛ እንዴት ነው ለሌሎች የእግዚአብሔር በረከት ምንጭ መሆን የምንችለው?
2. ከዮሴፍ ሕይወት ምን እንማራለን?

የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን አስታውስ

ከላይ የተመለከትነውን አጭር ገለጻ ለማጠቃለል ስናስብ መንፈሳዊ ሕይወታችንን ቆም ብለን እንድናስብ ይጠይቀናል: : ቆም ብለን እንድናስብ ስል መንፈሳዊ ሕይወታችንን መመርመር አለብን ለማለት ነው:: እግዚአብሔር በምድር ላይ ሲያስቀምጠን ዓላማ አለው:: ጌታችን የጸለየልንን ማስታወስ ያስፈልጋል:: "ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም። እኔ ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉም።" (ዮሐ. 17:15-16) ዛሬ ለኛ ምንም የማያሳስበን ከዓለም አይደሉም የሚለው ሐሳብ የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን ያቀጣጠሳት አርሱ ነው፤ እነርሱ ዓይኖቻቸው በኢየሱስ ላይ ነበር:: እነርሱ ኢየሱስ ሰው በመሆኑ የእግዚአብሔር ኃይልና አመራር በእርሱ እንዲገለጥ ስላየረጉት ሦስት ምርጫዎቹ ዕውቀት ነበራቸው:: እርሱን ለመምሰልና የእርሱን ምሳሌነት ለመከተል ቃሉን ያጠኑ ነበር፤ በመንፈስ ቅዱስ ይደገፉ ነበር፤ለጸሎት የተሰጠ የሕይወት ስልት ነበራቸው::

- **ለቃሉ**

የእግዚአብሔር ቃል ለኢየሱስ ሕይወትና ኑሮ

መመሪያው ነበር። በሕይወቱ የመጀመሪያ ሥፍራ የሰጠው ነገር ነበር። "ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም" (ማቴ. 4፡4) በቤተ መቅደስ በተገኘበት ጊዜም ኢየሱስ "በመምህራን መካከል ተቀምጦ ሲሰማቸውም ሲጠይቃቸውም" አገኙት (ሉቃስ 2፡46) ራሱን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ስላጠለቀ (ስለሞላ) "ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር።" (ሉቃስ 2፡52) በሰው ዘንድ ሞገስ ከማግኘታችን በፊት ከእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ ማግኘት ይቀድማል። ከሌሎች ጋር ለሚኖረን የወዳጅነት ግንኙነት መሠረቱ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን የወዳጅነት ግንኙነት ነው። የጥንት ክርስቲያኖች የክርስቶስን ፈለግ ይከተሉ ስለነበረ "በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።" (የሐዋ. 2፡42) የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት ለእነርሱ ታላቅ ደስታ ነበር።

- **ለመንፈስ ቅዱስ ኃይል**

ጌታ ሰው በሆነበት ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሞላ ነበር። "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥" (ሉቃስ 4፡18) እርሱ "መንፈስ ቅዱስ መልቶበት" (ሉቃስ 4፡1) ነበር። በምድራዊ አገልግሎቱ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ቁጥጥር ሥር ነበር።

ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ የመሞላትን አስፈላጊነት ያውቅ ነበር። ለዚህ ነው ደቀ መዛሙርቱን በኃይሉ እንዲሞሉ ያደረገው "በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥" (የሐዋ. 2፡4) ደቀ መዛሙርትም ይህ እንደሚያስፈልጋቸው ስለተረዱና ስላወቁ በየጊዜው ያለማቋረጥ ይሞሉ ነበር። (የሐዋ. 4፡8፣ 31) በመንፈስ

ቅዱስ ኃይል ተጽዕኖ ስር ስንሆን ግልጥነትና የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ይታይብናል። (ገላ. 5፡22) መንፈሳዊ ፍሬ እንድናፈራ የሐዋርያው ጳውሎስን ትዕዛዝ መከተል ያስፈልጋል "መንፈስ ይሙላባችሁ" (ኤፌ. 5፡18) ቶሎ ከኃጢአታችን ንስሐ ገብተን ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ማደስ በመንፈስ ቅዱስም ደጋግመን መሞላት ያለብን በጣም አስፈላጊ የሆነው ለዚህ ነው።

- **ጸሎት**

ኢየሱስ ከርስቶስ በጸሎት ተዋጊ ነበር። ለተከታዮቹ የሚጓዙበት/የሚከተሉት መንገድ አስቀመጠላቸው። አገልግሎቱን የጀመረው በአዳር ጸሎት ነቅቶ በመጸለይ ነው። "በነዚህም ወራት ይጸልይ ዘንድ ወደ ተራራ ወጣ፥ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ። በነጋም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ጠራ፥ ከእነርሱም አሥራ ሁለት መረጠ ደግሞም ሐዋርያት ብሎ ሰየማቸው፤" (ሉቃስ 6፡12-13) የሐዋርያቱን ምርጫ ያካሄደው በጥንቃቄ በተደረገ ጸሎት ነው።

ወደ አገልግሎት ከመሠማራቱ በፊት ሁልጊዜ ይጸልይ ነበር፤ "ማለዳም ተነሥቶ ገና ሌሊት ሳለ ወጣ ወደ ምድረ በዳም ሄዶ በዚያ ጸለየ።" (ማር. 1፡35) የዕለቱን አገልግሎት ካከናወነ በኋላም ይጸልይ ነበር፥ "ሕዝቡንም አሰናብቶ ይጸልይ ዘንድ ብቻውን ወደ ተራራ ወጣ። በመሸም ጊዜ ብቻውን በዚያ ነበረ።" (ማቴ. 14፡23)

የመጥምቁ ዮሐንስ ራሱን መቀላት ከአባቱ ጋር የጥምና ጊዜ እንዲኖረው አስፈልጎት ነበር። "ኢየሱስም በሰማ ጊዜ ከዚያ ብቻውን ወደ ምድረ በዳ በታንኳ ፈቀቅ አለ፤" (ማቴ. 14፡13) ችግር በገጠመው ጊዜ ሁሉ ወደ አባቱ ይጸልይ ነበር። "ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ

ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ አያለ ይጸልይ ነበር።" (ሉቃስ 22፡42) ለሚሰቅሉት እንኳን ፍቅሩን የገለፀው በጸሎት በማወጅ ነው። "አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ።" (ሉቃስ 23፡34) ይህ የመጨረሻ ጸሎቱ ነው።

ደቀ መዘመርቱ በጸሎት ሕይወቱ ስለተማረኩ ወደሱ መጥተው እንዲህ አሉት፥ "እንጸልይ ዘንድ አስተምረን" (ሉቃስ ፲፡፩) እርሱም አስተማራቸው እነርሱም በጸሎቱ ተቆራኝተው ቀሩ። "በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።" (የሐዋ. 2፡42) ይህም እኛ እንድንጸልይ ያበረታታናል። ጳውሎስም እኛን ሲያነሳሳን "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ።" (፩ቆሮ. ፲፡፩) ጴጥሮስ ሲያስታውሰን "የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና።" (፩ጴጥ. 2፡21)

የኢየሱስን ፈለግ የሚከተል ሰው በጊዜ አሸዋ ላይ የኢየሱስን ክብር ጥሎ ያልፋል። የኢየሱስን ፈለግ የተከተሉት ደቀመዘመርቱ ዓለምን ገለባበጡ። (የሐዋ. ፲፯፡6) ስለዚህ በሄዱበት ቦታ ሁሉ የለውጥ ኃይል ሆነው ነበር። ለጠፉትና ለምስኪኖቹ የሰላሙን ልሁል አስተዋወቁ። ለዘላለም ተስፋ የሌላቸውንና ያለክርስቶስ ለሆኑት ተስፋና ሰላምን አመጡላቸው። "በይሁዳም ሁሉና በገሊላ በሰማርያም የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ ታነጹም፤ በእግዚአብሔርም ፍርሃትና በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት እየሄዱ ይበዙ ነበር።" (የሐዋ. 9፡31)

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ልትመለከታቸው የሚገቡ ነገሮች፦

1) በሰላም ኖሩ
2) ታነጹም
3) በእግዚአብሔር ፍርሃት
4) በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት
5) ይበዙም ነበር

ዓለም በጽናት የምትፈልገው እንደዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ነው:: ለመንፈሳዊ መነቃቃት ጸልዩ: : እኔና አንተ የክርስቶስን ፈለግ ልንከተል ይገባናል:: የዓለማችንን መሠዊያ ለመለወጥ እግዚአብሔር እኔንና አንተን ይጠቀማል:: ጌታ ሆይ፤ እርዳን!!! የተባልነውን አድርገን ብንገኝ ጌታችን "መልካም፥ አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ" ብሎ ይቀበለናል:: እኛም ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር የድል በዓሉን አብረን እናከብራለን፤

"በመሥዋዕት እንደሚደረግ፥ የእኔ ሕይወት ይሠዋልና፥ የምሄድበትም ጊዜ ደርሶአል።መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።" (2ጢሞ. 4፡6-8)

❖

"እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው፣ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።" (ኤፌ. 3፡20-21) ሰማያዊ አባታችን እንደገና አነቃቃን ድንቅ በሆነው ልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፤ አሜን!!!

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ከጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ምን እንማራለን?
2. የተማርከውን እንዴት ተግባራዊ ታደርጋለህ?

በአንተ ላይ የሚነበበው ወንጌል

ተተርጉሞልኝ የሰማሁት ጣፋጭና ጥንታዊ ታሪክ አለ።
በማርቆስ፤ ሉቃስና ዮሐንስ ስለ ክርስቶስና ስለ ተልዕኮ
የሚከተለው ማዘጋጎ ቀርቦአል

አንተ ወንጌል እየጻፍክ ነው፤ በየዕለቱ አንድ ምዕራፍ፤
በምታደርጋቸው ድርጊቶች፤ በምትናገራቸው ቃላትና
ንግግርህ፤ ሰዎች አንተ የምትጽፈውን እያነበቡ ነው።
ውሸትና እውነት የሆነውን ሁሉ።
በአንተ በኩል የሚሰማው ወንጌል ምን ዓይነት?

የክርስቶስ ወንጌል ከማይለለቸውና ከእውነተኛው

ፍቅር ጋር በመደነቅ ሰዎች ያነቡታል።።
ነገር ግን በእንተ ስለሚጻፈው ወንጌል ሰዎች ምን
ይላሉ? ምን ያስባሉ?

ይህ አስደናቂ ታሪክ፣ የፍቅር ወንጌል፤ መለኮታዊ
በሆነው በክርስቶስ ሕይወት ከተንጸባረቀ፣ ይህ እውነት
ተደጋግሞ በእኔና በአንተ የሕይወት ታሪክ መነገር አለበት።።

ለራሱ ቅድሚያ ባለመስጠት እንደ መስታወት በሥራ
ቦታው የሚታይ
ባገኘው ለም አፈር ላይ ሁሉ የፍቅር አበባን የሚተክል
ከራሱ ራዕይ ወጥቶ በልቡ ያለውን
የእግዚአብሔርን አስደናቂ መልካምነት የሚናገር

አንተ በየቀኑ ለሰዎች ደብዳቤ እየጻፍክ ነው
የምትጽፈው እውነት ለመሆኑ መጠንቀቅ አለብህ
ይህ ጥቂት ሰዎች ሊያነቡት የሚችሉት ብቸኛው
ወንጌል ነው
በአንተ ላይ የሚነበበው ወንጌል

~ ደራሲው ያልታወቀ ~

ይህን ወይንም ሌሎች ጽሑፎችን ለማግኘት ወደሚከተሉት አድራሻዎች ይጻፉ፡-

Grace Evangelistic Ministries

በአሜሪካ፡-
P. O. Box 111999
Nashville, TN 37222
U.S.A
GEMworldwide.org

በአፍሪካ፡-
P. O. Box 583
Jos, Plateau State
NIGERIA
GEMAfrica.org

በእንግሊዝ፡-
GEMEurope.org
Office@gemeurop.org

ሞሰስ ሲ. አንዉቢኮ መንፈሳዊና አስተማሪ ናቸው፣ እ.ኤ.አ በ1997 ስተመሠረተው የአጋ መንፈስ አገልግሎት መሥራችና ፕሬዚዳንት ናቸው። ይህ አገልግሎት ለጠፋውና እየሞተች ላለቺው ዓለም ቤተ እምነት ሳይገድበው እምነት በክርስቶስ ብቻ የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ቅድሚያ በመስጠት ያገለግላል።

Moses C. Onwubiko

ቄስ ሞሰስ በአፍሪካ፣ በእስያ፣ በአውስትራሊያ፣ በመካከለኛ አሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ አሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ በመላክስኛ ምስራቅና በሰሜን አሜሪካ መንፈስን በማወጅና በማስተማር አገልግለዋል። እግዚአብሔር በክፈተላቸው በር ሁሉ ቆም ቢሆን በመሄድ እያገለገሉ ይገኛሉ።

እንተ ማህየ የሚለው ይህ ጽሑፍ በክርስቶስ ያለንን ማንነት የሚገልጽ ዘጠኝ የተለያየ ምልክታዎችን ያካተተ ነው። እያንዳንዱ መመሪያ በመጽሐፉ ቅዱስ ጥቅሶች የተደገፈ ነው።

ይህ ትምህርት በመጀመሪያ በሞሰስ ሲ. አንዉቢኮ የተሰጠው ለወጣቶች በሚልዋኪ አውስትራሊያ እ.ኤ.አ በ2014 ነው።

ክርስቲያናች ጥራም የሆነው መብታቸውንና የሚያገኙትን ፅድሎች ቢጠቀሙ በክርስቶስ ማንነታቸው ክርስትናን በሙላት ለመኖር ብቻ ሳይሆን ለራሳቸውና ለሌሎች በረከት መሆን ይችላሉ።

Jericho PRESS
Leading the Way Back to the Bible

ISBN 978-1-935222-22-4
90000
9 781935 222224